# ሆዳም የአማራ ምሁራን ሆይ! እስከ መቼ ተአባ የሻነው ትል ታንሳላችሁ?

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)

ዘግይተውም ቢሆን አንዳንድ የአማራ ምሁራን የለፍቶ አዳሪውና የአገር ገንቢውን አማራ ፍጅት ለማስቆምና ፍትህን ለመፈለግ መነሳታቸው ጎሽ የሚያሰኝ ነው፡፡ ዳሩ ግን አብዛኛው ሆዳም አማራ ምሁር አሁንም ተአባ የሻነው ትል አንሶ ድምጡን አጥፍቶ እንጀራውን እየጎሰጎሰና የበሬ ቆለጥ ስትከተል እንደዋለችው ዘልዛላ ቀበሮ የአማራ አስፈጂ "ሙሴዎች"ን በደም የተጨማለቀ ኮቴ ሲከተሉ እንደ ካድሬ ወንዝና ራያ ሁሉ መተከልና ወለጋ አማራ እየታረደ ነው፡፡ ሰሜን ሸዋ ተቆንጨራ የተረፈው አማራ፣ ንብረቱና ቅዬው እየነደደ ነው፡፡



አባ የሻነው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትል ታሪክ ደጋግመው ይተርኩልን ነበር፡፡ አባ የሻነው "ተትሏ እንማር!" ይላሉ ራሳቸውንም እንደተማሪ በመቁጠር፡፡ "ትሏ ዛፍ ለመውጣት ስትሞክር ወደቀች፤ አንድ በሉ፡፡ እንደገና ሞክረች ግን ነጠረች፤ ሁለት በሉ፡፡ አሁንም እንደገና ስትንጠለጠል ዘች አለች፤ ሶስት በሉ፡፡ ዘች ታለችበት ተነስታ እንደገና ተንጠለጠለች፤ ግን ተመልሳ እርፉቅ አለች፤ አራት በሉ፡፡ እርፉቅ ታለችበት ተነስታ አሁም ግንዱን በትንሹ ወጣች፤ ግን እንደገና ተንደባለለች፤ አምስት በሉ፡፡ ተተንደባለለችበት ተነስታ ተበፊቱ የበለጠ ርቀት ዛፉን ወጣች፤ ግን ተመልሳ ነጠረች፤ ስድስት በሉ፡፡ ተነጠረችበት ተነስታ ለሰባተኛ ጊዜ ስትሞክር ሰማይ የደረሰውን ዛፍ ምንም እንከን ሳይገጥማት ወጣችው" እያሉ ይተርካሉ ጨረቃ የመሰለ ፈገግታ እያሳዩና ሻሽ የመሰለ ጺማቸውን እያፍተለተሉ፡፡

ከትረካው በኋላም አባታችንና መምህራችን አባ የሻነው "በሰባተኛው ዙር ትሏ ለምን የተሳካላት ይመስላችኋል?" ብለው ሲጠይቁ "በሰባት ስላሴ ስለሚውል፣ ተስፋ ስላልቆረጠች ...ወዘተርፈ" እያልን እንመልሳለን፡፡ እርሳቸውም "እርግጥ ነው ተስፋ ያልቆረጠን ስላሴም ይረዳል!" ብለው የምንሰጠውን መልስ ሳያጣጥሉ "ትሏ የተሰካላት ተእያንዳንዱ ልምድ ትምህርት በመውሰድዋና ያደናቀፏትን መንገዶች ትታ ሌላውን በመከተልዋ ነው" ብለው ተልምድ የመማርንና የተለያዩ መንገድ የመከተልን ጠቀሜታ ያስተምራሉ፡፡

የአባ የሻነው ትል ያህል ተልምድ መማር ተስኗቸው ስለ ቦንድ እጃቸው ውሀ እስቲቋጥር የጣፉት፣ ላንቃቸው እስቲደርቅ የሰበኩት፣ ልሳናቸው ጥረቅም እስቲል የዘፈኑትና መቀመጫቸርውን እስቲያልባቸው ያረጠረጡት ህሊናቸው የሸጡ አለዚያም የተንዘላዘሉ

የለገሰ ቦንድ ካድሬዎች ነበሩ፡፡ አለዚያማ ሰይጣንና ለገሰን እንኳንስ ቆመው ሞተውስ ከዘልዛላ በቀር ማን ያምናቸዋል?

አያሌ ሆዳም የአማራ ምሁርና ተአባ የሻነው ትል አንሰው ለግማሽ ክፍለ ዘመን ሲደሰኩሩ የኖሩትን ድስኩር ዛሬም ይደሰኩራሉ፡፡ እንደ ዋለልኝ ያሉ ጭንጋፍ ምሁራን “አማራ ጨቋኝ ነው!” የሚለውን የሰይጣን መንፈስ አማራ ደጋግሞ አፈር ታስጋጠው ፋሽሽት ጣሊያን ተቀብለው ሲቀባጥሩ ስለኖሩ አሁን የአማራን ማህፀን እየቀደዱ ፅንስ ለሚያጠፉ ተአበደ አውሬም የከፉ እርኩሶች መከሰት አስተዋጥዖ አደረጉ፡፡ እንደ እነ ዋለልኝ የዛሬ ሆዳም አማራ ምሁራንም አማራን ሲያመክኑና ሲጨፈጭፉ እንደዚሁም እርስቱን በክልል ስም ሲነጥቁ የኖሩትን የትግሬ ነፃ አውጪ ገረድ ካድሬዎች ስብከት ተቋም እየቆጠሩ የአማራን ዘር ፍጅት እያባባሱት ይገኛሉ፡፡

ቲሞቲ ስናይደር የተባለ የየል ዩንቨርሲቲ ሊቅ እንደሚያስተምረው ዛሬ እሚታየው ምልክት የነገውን እውነታ ያሳያል*፡፡ ፕሮፌሰር ስናይደር እንደፃፈው ናዚዎች አይሁዳውያንን ለመጨፍጨፍ ሲወጥኑ  እንደ ለገጣፎና ሱሉልታ ገዥዎች በአይሁዶች ግድግዳዎች "አይሁድ በጀርመን ቦታ የለውም" የሚል ምልክት ለቀለቁ፡፡ ይኸንን የተለቀለቀ ምልክት ያነበቡ አይሁድ ምሁራን ግን እንደ ዛሬው አማራ ምሁራን "የጥቂት ጋጠ ወጦች ተግባር!" እያሉ አለፉ፡፡ እንደዚህ እይነቱ ጋጠወጥ ጋጠወጥን ከሚደግፍ ማህበረሰብ ውጪ እንደማይኖር ረሱ፡፡ በዚህ ችልታቸውም አይሁዳንን ሳያስጠነቅቁ በመደዳ አስጨፈጨፉ፡፡

ለገሰ ዜናዊ ወንበር እንደተፈናጠጠ የአማራውን ግድግዳ ትምክህተኛና ነፍጠኛ የሚል ቀለም ቀባው፡፡ የዚህን የቀለም ቅብ ምስጢር የአማራ ምሁራን መመርመር ሰነፉ፤ ሕዝቡም ችላ አለ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ለአማራ ምልክትነት የተቀቡትን ነፍጠኛንና ትምክህተኛን እነ ታምራት ላይኔና ስዬ አብርሃ በሃረር በአሩሲና በሌሎችም ሥፍራዎች ሰበኩ፡፡ ይኸንን ተከትሎም አማሮች በበደኖ ገደል ተወረወሩ፣ በአርባ ጉጉ፣ በአሩሲ ነገሌና በሌሎች ሥፍራዎች ታረዱ፡፡ ይህ እልቂት ለመጪው የአማራ የከፋ እልቂት ምልክት መሆኑን የተረዱት ክቡር ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስና ወጣት ጓዶቻቸው አማራን ለመከላከል ሲጥሩ አሽሚጣጭና ተመጻዳቂ የአማራ ምሁራን ዘመቱባቸው፡፡ እርሳቸው ሕክምና ተከልክለው አለፉ፤ እንደ ተሾመ ቢምረው ያሉ የትግል ልጆቻቸው ታፍነው እስከ ዛሬ የደረሱበት እንዳይታወቅ ሆኑ፡፡

የትናት በስቲያው የአማራ እልቂት ለትናንቱ እልቂት ለአማራ ምሁራን ቦቃ ምልክት በሆነ ነበር፡፡ የትናንትናው የእልቂት ቁስልም ዛሬ ለሚታየው የአማራ እልቂትና ስደት ፍንትው ያለ ምልክት በሆነ ነበር፡፡ የዛሬው መጠነ ሰፊ እልቂትና ስደትም ለነገው የከፋ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ቦግ ያለ ምልክት ሆኖ በታዩ ነበር፡፡ ነገር ግን ከትናት በስቲያና ትናንት ያየነውን የአማራ ቁስል ኢትዮጵያ፣ አንድነት፣ ተጋብተንና ተዋልደን በሚል ዝተት ፋሻ እየሸፋፈኑ ቁስሉን የባሰ አነፈረቁ፡፡ በዚህም ምክንያት ወልቃይት፣ ራያና ጉራፈርዳ ያየነው ሞትና መፈናቀል ዛሬ ምዕራብና መሐል ጎንደርን ፣ ምዕራብ ጎጃምን፣ ወሎንና ሙሉ ሸዋንም አዳረሰና አረፈው፡፡

ይህ አገር ምድሩን የሸፈነው ቁስል ነገ ለሚመጣው እጅግ የከፋ እልቂት ምልክት አድርጎ መዘጋቸት ሲገባ ይኸንን የነፈረቀ ቁስል አሁንም ወንድማማችነት፣ ተጋብተንና ተዋልደን በሚል ደም ማፍሰስን በማያቆም ፋሻ እየሸፈኑ አማራው ራሱንና ራሳቸውን መከላከል የማይችሉትን እንዳይረዳ እንደ ፀጋዬ ገብረመድህን የማይነጋ ሕልም ያልማሉ፡፡ ሲነጋም ህልሙን እንደ ከብት እያመነዠኩ ሲንዘላዘሉ ይውላሉ፡፡ ከመንዘላዘልም አልፈው ክቡር ፕሮፌሰር አስራትንና የትግል አጋር ልጆቻቸውን ያጠፏቸውን ጆሮ ጠቢዎች እያመለኩ ከእግራቸው ሲደፉና በካድሬነት ሲላላኩ ይውላሉ፡፡ አማራ ቢደራጅ ኖሮ ተዚህ አዘቅት እንደማይደረስ፤ ኢትዮጵያ እንዳትፈስ የአማራው ጥንካሬ ወሳኝ መሆኑን ይክዳሉ፡፡

ከአመታት በፊት አማራን በጠላትነት የፈረጁ ቡድኖች አማራውን አድቅቀው እንደፈለጉት ለማድረግ የጣሩት ለአንድ ኢትዮጵያና ለአማራ የቆመ ድርጅት እንዳይፈጠር በመከልከል ነበር፡፡ ለአንድነትና ለአማራ የቆመ ድርጅት በከለከሉባቸው ሃያ ሰባት ዓመታት እንወክለዋለን የሚሉትን ወጣት በፀረ-አማራነት ውቂያኖስ ዘፍዝፈው አይምሮውን በመበረዝ የፀር-አማራ መሰረታቸውን አጠናከሩ፡፡ ፀረ-አማራ መሰረታቸውን ካጠናከሩ በኋላ የለበጣ አንድነት ፖለቲካን አቀነቀኑ፡፡ በዚህ የለበጣ የአንድነት ፖለቲካም ኢትዮጵያ ሲባል ልቡ እንደ ለጋ ሺል የሚንፈራገጠውን አማራ እንደገና ጠለፉ፡፡ በዚህ ጠለፋም የአማራን አቅም የማድቀቅ ሴራውን ቀጠሉ፡፡ በፀረ-አማራ ስብከት ተነቅረው ያደጉት ሱሰኛ "ሙሴዎች"ና ባርጩማውን የለቀቁት ክፉዎች ግን ተዘራቸው ተጣብቀው ዘረፋውን ቀጠሉ፡፡

አማራ ጅቦች የማይሰሙትን "ኢትዮጵያና አንድነትን" ሲጨፍር ጅቦቹ ፀረ-አማራንና ክልልን ሲደልቁ ሰላሳ አመታት አለፉ፡፡ በዚህም ግርግር የዛሬዎቹ ጅቦች እንደ ትናንትናዎቹ ጅቦች የአገሪቱን ወታደራዊ ሐይል፣ ስልጣንና ምጣኔ ሐብት ያለ ሐፍረት

ጠራርገው ወስደው መሰረታቸውን አጠናክረው በመላ አገሪቱ አማራን ባለቤት እንደሌለው ጫካ ሲጨፈጭፉ ይውላሉ፡፡ የአማራ ቅርሶች እየፈረሱ ከቅርሶቹ የሚመጣውን ገንዘብ እነሱ ይልፋሉ፡፡ አማራ የታሪካዊ ቅርስ እሳት አጥፊ ከውጪ እየለመነ እነሱ የአገሪቱን የባንክ ገንዘብ በወንበዴ ክንፎቻቸው ያዘርፋሉ፤ የተረፈውንም ለቢሮና ለከተማ ውበት እያሉ ይዘርፋሉ፡፡ ይኽ ሁሉ ሲሆን የአማራ ምሁራን የበሬን ቆለጥ ስትከተል እንደኖረቸው ቀበሮ የሙሴአቸውን ስብከት ሲያዳምጡ ይውላሉ፡፡

አማራ ምሁራን የሕዝባቸውን እልቂት የሚተነብዩ ጉልህ ምልክቶችን እንዳላዩ አልፈው በአማራ ለደረሰው የዘር ማጽዳት ወንጀል አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ "አይሆንም ትተሽ ይሆናልን አስቢ" የሚባለውን ብሂል ዘንግተው "በእስቲ እንያቸው!" ዘልዛላ አስተሳሰብ ሕዝባቸውንና አገራቸውን ለዚህ አብቅተዋል፡፡ የትግሬ ነፃ አውጪን ፀረ-አማራ ግቦች መፈተሽ ሰንፈው አማራ ለሃያ ሰባት ዓመታት የገሃነብ ኑሮ ኖሯል፡፡ ይህ ቡድን ኤርትራን እንደሚያስገነጥል፤ ለም ምሬታችንንም ለጡት አባቱ ለሱዳን እንደሚያስረክብና የተፈውንም በክልል እንደ በሬ ቅርጫ እንደሚከፋፍል አማራ ምሁራን ለመተንበይ ሰንፈዋል፡፡ በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ራሱን ለመከላከል ያልተዘጋቸው አማራ እንደ ቅርጫ በተከፋፈለች አገር በማያውቀው "ሕገ-መንግስት" እንደ ደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች እንዲገዛ ተገዷል፡፡ ከሌሎች በከፋ መልኩ ሲታሰር፣ ሲገረፍ፣ ሲሰለብ፣ ሲሰደድ፣ በርሃብና በበሽታ ሲረግፍ ኖሯል፡፡ ፀረ-አማራ ገዥዎች የራሱን ባንዳ ልጆች ዛቢያ አድርገው ከደጁ ሞፈር ቆርጠዋል፤ ታሪኩና ቅርሱን አፈራርሰዋል፡፡ ከቅየው እያፈናቀሉ በእርዳታ ነፍሱን የሚያሳድር ሜዳ አዳሪ ሕዝብ አድርገውታል፡፡

ህሊና ያለውና ማፈርን የሚያውቅ አማራ ምሁር ለአምሳ ዓመታት በአማራ የደረሰው ግፍ እሳት እንዳየው ላስቲክ ሊያሽማቅቀው ይገባል፡፡ "በሞቴ አፈር ስሆን" እያለ እያጎረሰ ያሳደገውን ማህበረሰብ በጥቅም ታስሮ ወይም ሆዱን መርጦ በጅቦች ማስበላት መረገም መሆኑን ማጤን ይገባዋል፡፡ ፈገግ ሲል ሲል እየሳመ የታቀፈውን፣ ሲወድቅ ያነሳውን፣ ሲማር መቀነት እየፈታና ኪሱን እየፈተሸ ኮቢ የገዛለትን፣ ሲዳር ደግሶ የዘፈነለትንን፣ ሲሞት ፍታትና ተስካር የሚያወጣለትን ሙሉ በኩሉሔ ሕዝብ ለጅቦች አሳልፎ በመስጠቱ ሊፀፀት ይገባል፡፡ ከእነ ድንበሯና ክብሯ አገር ያስረከበውን ሕዝብ እንደ ይሁዳ ክዶ እልቂትን ካመጡበት ክፉዎች ጎን መቆም ሲኦል የሚከት ግዙፍ ኃጥያት መሆኑን ማመን ይኖርበታል፡፡

የአስኳላው፣ የቤተክህነትና የቤተ መስጊድ ምሁራን አማራ ዛሬ ከሚደርስበት እልቂት ወደፊት ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ መተንበይ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምሁራን በትናቱ ምልክት የዛሬውን መተንበይ ስላልቻሉ አማራ ዛሬ በመላ አገሪቱ እየታረደና እየተሰደደ ይገኛል፡፡ ምሁራን በዛሬው ምልክት የነገውን እየተነበዩ ስላልሆኑ አማራ ገና ብዙ ችግር ይጠብቀዋል፡፡ እንደ አለመታደል የአማራ ምሁራን ከዛሬው ምልክት የነገውን በመተንበይ ፋንታ በሱሰኛ የላቲን ሙሴዎች ቀንበር ተጠምደው በካድሬነት ሲያገልግሉ ይታያል፡፡ ለአማራ ህልውና አስተዋፅኦ ከማበርከት ይልቅ አማራን ለመታደግ የሚፍጨረጨሩትን ወጣቶች በማብጠልጠልና በመጥለፍ ተጠምደዋል፡፡

ወጣቶቹ ለዚህ መከራ የተዳረጉት እኛ ታላላቅ ወንድሞችና አባቶቾች ሐላፊነታችንን ስላልተወጣን መሆኑን የላቲን ሙሴዎች ተከታዮች ዘንግተዋል፡፡ እኛ ሐላፊነታችንን ብንወጣ ኖሮ ወጣቶቹ ሥለሰማይና ሥለምድር ሲመራመሩ ይውሉ እንደነበር ማስተዋል ተስኗቸዋል፡፡ ወጣቶቹ የህልውና ትግል የሚያደርጉት እኛ ከከተትናቸው ገደል ለመውጣት መሆኑን የሚያመልኩት የላቲን ሙሴ አስረስቷቸዋል፡፡

የህልውና ትግል የሚያደርገውን ወጣት የአማራ ምሁራን እየጠለፉ ከሚጥሉባቸው ወጥመዶች አንዱ "ኢትዮጵያ፣ ዜግነት፣ ማህበራዊ ፍትህ!" የሚባል ዘፈን ሆኗል፡፡ ይኸንን ዘፈን ማዘውተር አማራን ለሰላሳ ዓመታት አሳርዷል፡፡ እንዲያውም በዚህ ዘፈን ወጣቱን መጥልፍና መጣል አማራው ለሌላ ዙር የዘር ማጥራት አጋልጦ እንደመስጠት ይቆጠራል፡፡

ከዚህ በፊት "ኢትዮጵያ፣ አንድነት፣ ዜግነት" እያሉ በሰፋፊ አዳራሽ የዘፈኑ ፓርቲዎች አማራን በበደኖ ገደል ከመወረውር፣ በአርባ ጉጉ ከመታረድ፣ ከወልቃይት፣ ከራያ፣ ከመተከልና ከጉራ ፈርዳ በችፍርግ ከመጠረግ አድነዋል ወይ? ኢትዮጵያ፣ ዜግነት ማህበራዊ ፍትህ እያሉ እሚደልቁት ቡድኖች ዛሬ አማራ ካድራ ወንዝ፣ ሀረር፣ ወለጋ፣ መተከል፣ ከሚሴ፣ ሸዋና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች ሲታረድና ሲሰደድ እንኳን ሊከላከሉ ድርጊቱን የሚያወግዝ ትንፋሽስ ቱስ ብሏቸዋል ወይ? ሲሞዳሞዱ የሚውሉት ከገዳዮችና ከአስገዳይዎቹ ጋር አይደለም ወይ?

ኢትዮጵያ፣ አንድነትና ዜግነት በሚል ፋሻ የአማራን ቁስል እየሸፋፈኑ አማራ ሳይደራጅ በተደራጁ ሐይሎች እንዳለፉት አርባ ሁለት ዓመታት እንዲያልቅ ማድረግ በምድርና በሰማይ የሚያስጠይቅ የወንጀሎችና የኃጥያቶች ቁንጮ አይደለም ወይ? የአማራን

የመከላከል ሐይል ለማዳከም የዜግነት ፓርቲ አቋቋምን ብለው የውሸት መሐላ በየወንዙ ከሚማማሉት አብዛኞቹ በድርጅቶቻቸው አማራን አስበልተው በመጨረሻም አማራን ከበላው ድርጅት እግር የወደቁ ይሁዳዎች አይደሉም ወይ? እነዚህ ይሁዳዎች አማራ ነገ የሚደርስበትን ችግር ይከላከላሉ ተብሎ ይጠበቃል ወይ?

ለስድሳ ዓመታት በፀረ-አማራ መንፈስ የተደራጁ ክፉ ቡድኖች ተከታዮቻቸውን በአንድ ፊሽካ ሲነዱ አላየንም ወይ? ትናንት ነፍጠኛና ትምክህተኛ የተቀባው አማራ ዛሬ ደሞ እንደ ናዚ ዘመን አይሁዳውያን "መጤና ሰፋሪ" የሚል ቀለም አልተቀባም ወይ? ታዲያ በዚህ ዘመን አማራ እንዳይደራጅ ጋሬጣ መሆን የሂትለር ተባባሪ ከመሆን ይለያል ወይ?

በአማራ መቃብር ሪፐብሊክ ለመገንባት በተነሳው ለገሰ ዜናዊና በቅኝ-ግዛት ታሪክ አቀንቃኙ ላቲኑ ሌንጮ ለታ ተሰብከው ያደጉ ከአርባ ዓመት በታች የሚገኙ ወጣቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ አህዳዊ ፖለቲካ ይመጣሉ ብሎ ማሰብ ግብዝነት አይደለም ወይ? እንኳን የለገሰና የሌንጮ ተከታዮቹ መራራ ጉዲናስ ተአክራሪ አማራ ጠሎች ጋር እግሩን አምቧትሮ ሲቆም አላየነውም ወይ?

የአማራ ምሁራንን ከንቱ ድስኩርና ስብከት እየሰማ ያልተደራጀው የአማራ ወጣት ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ከመከራ ወጥቶ ያውቃል ወይ? የአማራ ምሁራንን ከንቱ ስብከት ተማምኖ ወጣቱ ዛሬም እንደ ትናንቱ ለመገረፍ፣ ለመሰለብ፣ ለመሰደድ፣ ከትምህርት፣ ከጤናና ከስራ ተገሎ ለመኖር እጁን አጣጥፎ ይቀመጥ ወይ? ድርጅት እንደ አፈር ሲቆልሉና መልሰው ሲንዱ፣ ፓርቲ እንደ ፍሪንባ ሲተለትሉና እንደ ክትፎ ሲከታትፉ የኖሩ ፖለቲከኞችን ዛሬም አምኖ ራሱን ተመከላከል ይታቀብ ወይ? አማራ ሲታሰር፣ ሲገረፍና ሲሞት የኖረው በእነዚህ ፓርቲ እንደ ጪቃ ሰርተው በሚያፈርሱ ፖለቲከኞች አይደለም ወይ? እነዚህ ፓርቲ በመሰንጠቅ እጥፍ ድርብ ፒ ኤች ዲ ያላቸው ከሀዲ ፖለቲከኞች እንኳን የኢትዮጵያን ሕዝብ ራሳቸውንስ አንድ ያደርጋሉ ወይ? እነዚህ ፖለቲከኞች እንደ ሳሙኤል አወቀ ተቀጥቅጠው የተገደሉትን በማተባቸው አዳሪ ወጣቶችና በድርጅቶቻቸው ስም የተሰለቡትንና አካለ ስንኩላን የሆኑትን ዜጋዎች ክደው ዛሬ ከገዳዮችና ከገራፊዎች የሚሞዳሞዱ ይሁዳዎች አይደሉም ወይ?

አማራ ምሁራን ሆይ! **አኩርሽምንማ** ከአማራ በላይ የሚወድ ነበር ወይ? "ኢትዮጵያ፣ ዜግነት፣ አንድነት፣ ፍትህ!" የሚባሉትን አኮርሽሞች እንደ በኩር ልጅ ከአማራ በላይ እያሞላቀቀና እያሞካሸ ጠርቶ የማይጠግባቸው አለ ወይ? አማራ ከክብሩ ዝቅ ብሎ

ከኢዮብ የከፋ መከራ የተቀበለው እነዚህን እንደ በኩር ልጁ ጠርቶ የማይጠግባቸውን አኮርሸሞች በመውደዱ አይደለም ወይ? እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲን እንደ ፍልጥ በመተርተር የሚታወቁት ፖለቲከኞችስ አማራን ዳግም ሊያዘናጉና ሊያልቡ የተነሱት ይኸንን የአማራን ቅዱስ ባህሪ እንደ ድክመት ቆጥረው አይደለም ወይ?

አማራ ምሁራን ወይ! በዓለም ማህበራዊምና ኢኮኖሚያዊ ፍትህን ለማስፈን የቻለ ቡድን የለም፡፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ በምድር ሰፍኖም አያውቅም፡፡ ወደፊትም ሕዝብ እየበዛና  እንደ መሬትና ውሀ ያሉ መሰረታዊ እሴቶች እየጠበቡና እያነሱ በሄዱ ቁጥር የማህበረሰባዊና የኢኮኖሚ ስርጭቱ ከፍትህ እየራቀ የሚሄድ ነው፡፡ እስካሁን እንደታየው ዓለም ወደ ማህበራዊ ፍትህ ፊቷን የምታዞረው በማህበረሰቡ መካከል የጉልበትና የጥበብ ሚዛን ሲኖር ብቻ ነው፡፡ አንዱ እንደ ገመድ ወፍሮ ሌላው እንደ ክር ቀጥኖ ማህበራዊ ፍትህ እያሉ ቢተርቱ ህጻንም አምኖ አይቀበልም፡፡ ዓለም ተቻችላ ያለችው በሐይል ሚዛን ነው፡፡ አገርም ተቻችሎ እሚኖረው በኃይል ሚዛን ነው፡፡ የፍትህ ስብከት ህፃናትን የሚጨፈጭፍና የሚሰልብ ጭራቅን ግብር ያከፋዋል እንጅ አያሽለውም፡፡ ምክር የላም አሽናፊን እንደ ፌንጣ  የበለጠ ያቅበጠብጠዋል እንጅ አያስታግሰውም፡፡

ጠንካራ ዲሞክራሲና ሕግ አላቸው በሚባሉት አውሮጳና አሜሪካ ሳይቀር የኢኮኖሚና የማህበረሰባዊ ፍትህ ዛሬም የለም፡፡ ቀለማሙ ሕዝብ ሊፈጥር በሞከረው የኃይል ሚዛን ትግል ከቤት ባርያነት ቢላቀቅም ዛሬም የውጪ ባርያ ነው፡፡ ባርያው ያደረገው መጠነኛ ትግል ፈቀቅ ያደረገው ከቤት ወደ ውጪ ብቻ ነው፡፡ ይህ የውጪ ባሪያ ዛሬም መንገድ፣ ሽንት ቤት፣ ሆስፒታልና ቢሮ ጠራጊ ነው፡፡ ይህ የውጪ ባሪያ ዛሬም የጡረተኞችንና የአካለ ስንኩላንን ሽንት እየጠረገ የሚጦር ባርያ ነው፡፡ በየትኛውም ዓለም የማህበራዊ ፍትህ ያለው ከወረቀትና ከውሸታም ፖለቲከኞች ላንቃ ብቻ ነው፡፡

ዓለምን ሲገዛት የኖረው፣ ዛሬም የሚገዛት ወደፊትም የሚገዛት የአካላዊና የአይምሮ የበላይነት ወይም ጉልበት ነው፡፡ ዓለምን የሚያሽከረክራት የከዳነው የመለኮት ትዕዛዝ ሳይሆን የተቀበልነው የሳጥናኤል መንፈስና ዳርዊን የቀመረው የጉልበት አሰላለፍ ብቻ ነው፡ ፡

አማራ በአጥንቱ ግድግዳነትና በደሙ ምርግነት ባቆማት አገሩ ቤቱ በግፈኛ እየፈረሰና ንብረቱ እየተቀማ ተገድሎ በጅምላ በግኢደር ታፍሲ የሚቀበረው የውጪ ጠላትን ያንበረከከበትን የጉልበትና የጥበብ ሕግ ለውስጥ ጠላቱ ስላልተጠቀመበት ነው፡፡ አማራ

እየተገደለ ገደልና ሽንት ቤት የተጣለው ሊበላው የመጣውን ጅብ ኢትዮጵያ፣ አንድነት፣ ዜጋ፣ ፍትህ በሚባሉ ለጅብ በማይገቡ ጽንሰ-ሐሳቦች ሊመልስ በመሞከሩ ነው፡፡ አማራ ህልውናው አስጊ ደርጃ የደረሰው ምሁሮቹ ለጅብና ጭራቅ በማይገቡ ቋንቋዎች ቀፍድደው እንዳይደራጅ ስለከለከሉት ነው፡፡ ዛሬም አማራን ለእልቂት የሚያጋልጡት ከትናንቱ ምልክት ዛሬን ከዛሬውም ነገን መተንበይ የማይችሉ ከአብራኩ የወጡ ድስኩራም እድሜ ጠገብ ምሁራን ናቸው፡፡

አማራ ምሁራን ሆይ! አማራን በጠላትነት የፈረጁ ሐይሎች እስተ አፍንጫቸው ታጥቀው አማራን በየሥፍራው እየፈጁት ሳለ አማራ ራሱን እንዳይከላከል ገንዞ መያዝ ለባሰ እልቂት መዳረግ መሆኑን እንዴት አጣችሁት? በሂትለር ዘመን የአይሁዳውያን ግድግዳ ይቀባ እንደነበረው ዛሬ የአማራ ቤት በመጤና የሰፋሪ ቀለም እየተቀባ ሲጨፈጨፍ ምነው ባቄላ እንዳነቀው ዶሮ ጭጭ ማለትን መረጣችሁ? አማራን በጠላትነት ፈርጀው ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ከስድሳ ዓመታት በላይ የሰበኩ ክፉዎችን በማህበራዊ ፍትህ ስብከት መመለስ የሞተን አስነስቶ በእግሩ የማስኬድን ያህል ከባድ መሆኑ እንዴት አጣችሁት?

አማራ ምሁራን ሆይ! የአባ የሻነው ትል ሰባት ጊዜ ሰባት የተለያዩ መንገዶች ሞክራ ዛፍ ለመውጣት ስትበቃ ምነው እናንተ ለሃምሳ ዓመታት በተሽመደመዳችሁባት አንድ መንገድ እያነከሳችሁ አማራን ማስፈጀቱን ቀጠላችሁ? ከሃምሳ ዓመታት በኋላም ምነው ከትሏ ትምህርት መቅሰም አቃታችሁ? እስከ መቼ ተአባ የሻነው ትል ታንሳላችሁ?

* on tyranny: Twenty Lessons from The Twentieth Century chapter 4

ተጨማሪ ጽሑፎች፡

**1. A Message to Amara Elites: Never Allow Ethnic Cleansing of Amara Again!**
https://www.zehabesha.com/a-message-to-amara-elites-never-allow-ethnic-cleansing-of-amara-again/?fbclid=IwAR39-VVEyK9B3K4qyv40xVyKLFAQ4yQd3NZ5gdVLLEIf-OL3BW8pyuuTAWI
**2. Please Stop Predisposing Amaras to Continue Perishing in Cities and Rural Areas!**
https://www.zehabesha.com/please-stop-predisposing-amaras-to-continue-perishing-in-cities-and-rural-

areas/?fbclid=IwAR0Qk8s_L_KBHRRXn9o_pr0Uu5fVnyDhkI4MuXMye0enMnRcpwfc2owSorI

3. The Ethiopian Elites Have Failed to Follow The Principles of Our Forefathers! https://www.zehabesha.com/the-ethiopian-elites-have-failed-to-follow-the-principles-of-our-forefathers/?fbclid=IwAR2vDSOkwZ2-A8HUa-iajOYFrvb49Z2rdD62jLkfLA_T7p2V6vWcco9gEIk

4. **በስልጣን ሰክሮ ያበደን ካድሬ ውይይትና ምክር ሊፈውሰው ይችላልን?**
**https://welkait.com/?p=19399&fbclid=IwAR1PGGrvShRVdWUA5_-QmXlhonXcdrFDR-J6pIJv3LWBYPyRq9vwJLcWYYY**

5. **አማራ ሆይ! ምን እስኪሆን ነው የምትጠብቀው?**
**https://welkait.com/?p=17552&fbclid=IwAR1eqGmFZYQ_aO5tKOaJXsFZzW--Hi6PULfLQMJuSvh067CnTy-MMzFduuo**

6. **ጨቋኙ አማራ ይኸው ነው!**
**http://amharic.abbaymedia.info/archives/29664?fbclid=IwAR0e_LnjBSS5a32RXriIAS3_laU5kG-7WR3yaAZLzygplOiqXGeGFxecv54**

7. **አማራ ዳግም አትታለል እንደ ላሜ ቦራ!**
**https://welkait.com/?p=16336&fbclid=IwAR3TucrZU-L98xi7BHvmfy72coFWall47VWRKXYQs3OAlGT3_yttzFuqEns**

8. **ወጣት ሆይ! እደግ! ተመንደግ! – በላይነህ አባተ**
**https://www.zehabesha.com/amharic/archives/94987?fbclid=IwAR16KT0YJujEAGRuw2Qum3Thw7GD6WvIp8TfLCXeETm6ptbZ2BRBzqJiL2g**

9. ወጣት ሆይ! ለህልውናህም ሆነ ለክብርህ ወደ ባህልህ!
http://ethioforum.org/amharic/%E1%8B%88%E1%8C%A3%E1%89%B5-%E1%88%86%E1%8B%AD-%E1%88%88%E1%88%85%E1%88%8D%E1%8B%8D%E1%8A%93%E1%88%85%E1%88%9D-%E1%88%86%E1%8A%90-%E1%88%88%E1%8A%AD%E1%89%A5%E1%88%AD%E1%88%85-%E1%8B%88%E1%8B%B0/?fbclid=IwAR0tsEDbDAQaE5BkeeJpzHCv3j30RxoxKtsV4ybfgBg8PTatn0eJmmIQSz0

10. አማራ ሆይ! ሰው እንሰሳም ነው!
https://welkait.com/?p=19311&fbclid=IwAR15eJVKUJ_b6SBFd-Sz8_mJ4wDOCGfJ4a6gVy8HQJdTigeXypyWG7KTwSc

11. የአማራ ጨቋኙ አቀንቃኞች እምቢኝ አረፋውን ባህሪ!
http://ethioforum.org/amharic/%E1%8B%A8%E1%8A%A0%E1%88%9B%E1%88%AB-%E1%8C%A8%E1%89%8B%E1%8A%99-%E1%8A%A0%E1%89%80%E1%8A%95%E1%89%83%E1%8A%9E%E1%89%BD-%E1%8A%A5%E1%88%9D%E1%89%A2%E1%8A%9D-%E1%8A%A0%E1%88%A8%E1%8D%8B%E1%8B%8D/?fbclid=IwAR06hGmzfyvYp0pamjEv2M4Oo3U4k5Lh1ucqE_NFHVb1MGmMet2mr-YUpeU

12. አማራ ከጅብ መንጋጋ ተላቆ ከእስስት አፍ ገብቷል! (በላይነህ አባተ)
https://www.satenaw.com/amharic/archives/64345?fbclid=IwAR186W_UWnfZoS9_NhCKQ6hRHdx-c_W7HT3r0oLNVu1fzZhmad9LwyAsndY

13. ለአባትዮው ለገሰ ቦንድ ለልጁ ፓስተር አቢይ ፈንድ!
https://welkait.com/?p=19088&fbclid=IwAR1mqyYRoNVg3ZCVPhEbSzxYZU3FGf1QH5siUhRwKdaKla-0Q6Ly4lKx7dY

14. ሕዝብ እንዲሰማህ ሰፊ አፍ ይኑርህ!
http://www.zehabesha.com/amharic/archives/94149?fbclid=IwAR0531t6KCkF-TywMIFjVmqx-jZyabuh_Ourw5vqSlrFVACc8DH6ROXJgA8

15. በአማራ ሰማእታት የተፈጠመው ግፍ በቅዱሳን ሐዋርያት ከተፈጠመው ግፍ ይከፋል! (በላይነህ አባተ)

https://www.satenaw.com/amharic/archives/63706?fbclid=IwAR1Jz8X8rmn5Sxgbt9b-r_7VJ5P6stU0n79czhwp83hq9kB19i5_hiBhDRc
16. ይሁዳ ክርስቶስን በሰላሳ ዲናር ሸጠው! (በላይነህ አባተ )
https://www.satenaw.com/amharic/archives/61148?fbclid=IwAR2x5wsTnwsME1ckDTJJfBg1VI_TgjoH0Wvba8dq_PjEyqkEcm32hq2cu5I
17. Urgent Message to Amara Elites: Speak Up Against The Ethnic Cleansing of Amara!
https://www.zehabesha.com/urgent-message-to-amara-elites-speak-up-against-the-ethnic-cleansing-of-amara/?fbclid=IwAR1XeFACxW_EiJB03BjvYZrMtNL0J7TFUgBO9OMGAGpGvGOsDQmryq4UJ4c